INJIBARA UNIVERSITY

# በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ

# የስርዓተ ጾታ ፖሊሲ

ብርሃኑ በላይነህ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ

2010 ዓ.ም

23/09/10

ስር/ጾታ/ፖሊሲ ቁ.1/2010

## የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የስርዓተ ጾታ ፖሊሲ

### መግቢያ

የእንጅባራ ዩኒቨረሲቲ በ2025 በኢትዮጵያ ተመራጭ በአፍሪካ ታዋቂ ዩኒቨረሲቲ ለመሆን ራዕይ አስቀምጧል፡፡ ከዚህ ራዕይ ለመድረስ የፆታ እኩልነትን ማስፈን፣ ጾታዊ ትንኮሳን እና ጥቃትን መከላከል እና ማስወገድ እንዲሁም ሴቶች ጾታን መሠረት በማድረግ የደረሰባቸውን ታሪካዊ እና ባህላዊ አድሎ ለማካካስ ድጋፍ (Affirmative action) መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ዩኒቨርሲቲው በሕገመንግስቱ እና ሀገራችን ተቀብላ ባፀደቀችው ዓለም አቀፍ በሴቶች ላይ የሚፈፀመውን ማንኛውም አይነት አድሎ ለማስወገድ የወጣው የቃል ኪዳን ሰነድ እንዲሁም ትምህርት ሚኒስተር ባወጣው የስርዓተ ጾታ ፖሊሲ (Harmonized Gender policy) ላይ የተካተቱትን ዕንስ ሐሳቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት አቅጣጫ ማስቀመጥ ይጠበቅበታል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ሁለቱ ጾታዎች በተለይ ሴቶች ሙሉ አቅማቸውን እንዲጠቀሙና ለራሳቸው፣ ለዩኒቨርሲቲው እንዲሁም ለሃገራቸው ማበርከት ያለባቸውን አስተዋጾኦ ማበርከት እንዲችሉ ምቹ የስራ፣ የመማሪያ እና የማሕበራዊ አካባቢ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ያምናል ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የዩኒቨርሲቲው የስርዓተ ጾታ ጽ/ቤት ወጥ የሆነ ፖሊሲ እና መመሪያ ማዘጋጀት አስፈልጎታል፡፡

በመሆኑም፣

- ዩኒቨርሲቲው ለሁለቱም ጾታዎች እኩል ዕድል በማመቻቸት ፆታዊ ትንኮሳን፣ ጥቃትን እና አድሎን ማስቀረት በማስፈለጉ፣
- ዩኒቨርሲቲው ሴቶች የሚደርስባቸውን ችግር ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ችግር ሲያጋጥማቸው የሚያሳውቁበት አገልግሎት መዘርጋት ያለበት በመሆኑ፣

ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ

ፕሬዝዳንት

- ማንኛውም የዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ በሴቶች ላይ ፆታዊ ትንኮሳ፣ ጥቃት እና አድሎ መፈፀም ክልክል መሆኑን በሚገባ በማሳወቅ እና እነዚህን መመሪያዎች የተላለፈ ቢኖር እርምጃ እንዲወሰድ በማስፈለጉ፣
- ዩኒቨርሲቲው የሚፈጽማቸው ግንኙነቶች የስርዓተ ጾታ እኩልነትን ከግምት ውስጥ ያስገቡ እንዲሆኑ ይህን ፖሊስ አውጥቷል፡፡

*የስርዓተ ጾታ ፖሊሲ አስፈላጊነት*

ዩኒቨርሲቲው የስርዓተ ጾታ ችግሮችን ለመፍታት በስርዓተ ፆታ ጽ/ቤቱ የሚሰሩ ስራዎች ወጥ በሆነ ፖሊሲ እና መመሪያ በመደገፍ ዘላቂነት እና ወጥነት ያላቸዉ እንዲሆኑ ለማድረግና አጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው የሚመራበት የስ/ጾታ ፖሊሲ በማዘጋጀት የተሻለ ስራ በስርዓተ ፆታ ጉዳዮች ላይ በመስራት ፆታዊ እኩልነትን ለማረጋገጥ እና ጾተዊ ፍትህ ለማስፈን ይህን ፖሊሲ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

*የፖሊሲው ግብ ( Goal)*

ዩኒቨርሲቲው ፆታን መሠረት ያደረገ አድሎ፣ትንኮሳ እና ጥቃት የሌለበት፣ የሴት ተማሪዎች መምህራን እና ሠራተኞች መብት እና ክብር የተጠበቀበት ብሎም በትምህርት፣ በስራ በምርምር እንዲሁም በማሕበረሰብ አገልግሎት እና አመራር ዘርፍ ፆታዊ እኩልነት የሰፈነበት የምርምር ተቋም ማድረግ የፖሊሲው ዋና ግብ ነው፡፡

*የፖሊሲው ዓላማ (Objectives )*

1. ሴት ተማሪዎችን በትምህርታቸው በማብቃት የሴት ተማሪዎችን የማቋረጥ መጠን መቀነስ :
2. ፆታዊ ትንኮሳ እና ጥቃትን ማስወገድ ፣
3. የሴት መምህራንን ቁጥር ከወንዶች እኩል ማመጣጠን፣
4. የሴት መምህራን እና ሠራተኞች የሃላፊነት ተሳትፎ ማመጣጠን፣

ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

እነዚህን ግቦች እና ዓላማዎች ከዳር ለማድረስ የስርዓተ ፆታ ጉዳዩን ከዩኒቨርሲቲው ሦስት ዋና ዋና የስራ ዘርፎች (Pillars) ማለትም ከምርምር፣ ከመማር ማስተማር እና ከማሕበረሰብ አገልግሎት ጋር የሚያያዝ ወጥ የሆነ ፖሊሲ መኖር አለበት ፡፡

*1. በመማር ማስተማር*

1.1. ሴት ተማሪዎችን ማብቃት የእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል መምህር /መምህርት ሃላፊነት በማደረግ ከብቃት መገምገሚያ መስፈርቶች አንዱ እንዲሆን ማድረግ ፡

1.2. እያንዳንዱ ፋኩሊቲ /ኮሌጅ /ት/ቤት/ኢንስቲትዩት ወዘተ. ለሴቶች የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት ካውንስለሮችን መመደብ እንዲሁም ሴቶችን ለማብቃት የሚያገለግሉ ሌሎች አገልግሎቶች መስጠት ግዴታ እንዲኖርባቸው ማድረግ ፡፡

1.3. ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ ፆታዊ ትንኮሳ እና ጥቃቶችን ከመፈፀም እንዲቆጠቡ ብሎም እንዲከላከሉ ግዴታ መጣል፡፡

1.4. ልዩ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ሴት ተማሪዎች ጫና ሲፈጠርባቸው ከትምህርት ገበታቸው እንዳይሰናከሉ ዩኒቨርሲቲው የተቻለውን ማድረግ ፡፡

1.5. ሴት ተማሪዎች በመረጡት ት/ክፍል ገብተዉ እንዲማሩ ልዩ ድጋፍ ማድረግ ፡፡

1.6. የሚዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት ጀንደርን መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲዘጋጅ፣ማድረግ፡፡

2. **በምርምር**

2.1. ዩኒቨርሲቲው የሚያካሄዳቸው ምርምሮች የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ከግምት ውስጥ ለማስገባት የሴቶችን ችግር የሚፈቱ ምርምሮችን ማበረታታት፣

2.2. ዩኒቨርሲቲው በስርዓተ ጾታ ትኩረት ላደረጉ የምርምር ስራዎች ማበረታቻ መስጠት፣

2.3. ሴቶች በምርምር ዘርፍ እንዲሳተፉ ማበረታታት እና አቅማቸውን ማሳደግ

ብርሃኑ [signature] አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

F.D.R.E Ministry Of Education Injibara University

3. በማሕበረሰብ አገልግሎት

3.1. የተለያዩ የማቋቋሚያ ማዕከሎች (Incubation centers) በማቋቋም መብቃት ያልቻሉ ሴት ተማሪዎችን የተለያዩ የሙያ ስልጠናዎች በመስጠት ከተለያዩ አካላት ጋር በመመካከር እንዲቋቋሙ ማድረግ::

3.2. በችግር ምክንያት ትምህርታቸውን መከታተል ላልቻሉ ሴት ተማሪዎች ጊዜያዊ ችግራቸውን ለመፍታት የሚችሉ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ድጋፍ ማስጠት ::

3.3. ለዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ ስርዓተ ጾታን የሚመለከቱ ትምህርቶችን በመስጠት የሕብረተሰቡን የተዛባ አመለካከት መቀየር::

*4. በሃላፊነት ቦታ ሴቶችን ማሳተፍ*

4.1. በዩኒቨርሲቲው መዋቅር ውስጥ በሚገኙ የሃላፊነት ቦታዎች እና በሌሎች ማሕበራዊ አገልግሎቶች እና እንቅስቃሴዎች የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ::

4.2 በፌዴራል መንግሥት ሴቶችን ለማብቃት የሰጠውን አዎንታዊ የድጋፍ እርምጃ (Affirmative Action Policy) በትክክል እንዲተገበር ማድረግ ::

*5. በዕቅድ እና ሪፖርት ውስጥ ስርዓተ ጾታን ስለማካተት*

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚገኙ ማንኛውም የስራ ክፍሎች በሚያወጡት ዕቅድ እና በሚያቀርቡት ሪፖርት ላይ ስርዓተ ጾታን በተመለከተ እንዲያካትቱ እና የስራ ሪፖርቱ ውጤታማነት ስርዓተ ፆታን ማካተቱ እንደ አንድ መለኪያ እንዲሆን ማድረግ ::

*6. ስለበጀት አመዳደብ*

ዩኒቨርሲቲው ለስርዓተ ጾታ ጉዳዮች አቅሙ በፈቀደ መጠን በቂ እና ተገቢ በጀት ይመደባል ይህንን በጀትም ለታሰበለት አላማ እንዲውል ያደርጋል ::

F.D.R.E Ministry Of Education Injibara University

ጠላይ አቡኔ (ፕ/ሊ)
ፕሬዝደንት

## 7. ስርዓተ ጾታን ስለሚመለከቱ ባለ ድርሻ አካላት

ዩኒቨርሲቲው አካባቢያዊ፣ ባህላዊ/ሃገራዊ/ እና አለም አቀፋዊ ስርዓተ ፆታን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር፣ በመመካከር እና በመደጋገፍ አብሮ ይሠራል።

ይሕ ፖሊሲ ሴኔቱ ካፀደቀበት ከግንቦት 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት